መልእክት አራት

## የታቦቱ እና የማደሪያው ድንኳን ታሪክ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ሳሙ. 4፡1—7፡2

**I. ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ-ሰው፣ እንደ እግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን የሕያው እግዚአብሔር ቤት የሆነችው የቤተ ክርስቲያን እውነታ፣ የእግዚአብሔር እና ሰው የጋራ መኖሪያ ለመሆን እግዚአብሔር ወደ እኛ ውስጥ ይገነባ ዘንድ እና እኛም ወደ እርሱ ውስጥ እንገነባ ዘንድ ክርስቶስን ማትረፍ እንድንችል እርሱ አግኝቶናል–ፊልጵ. 3፡8፣ 12-14፤ ዮሐ. 1፡14፤ ራእ. 21፡2-3፤ 7፡15፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ዮሐ. 14፡2፣ 23።**

**II. ወደ ክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ለመግባት፣ የታቦቱን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ማየት አለብን፦**

*ሀ.* ታቦቱ ኢኮኖሚውን ለማከናወን መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት የሦስታንዱ አምላክ መገኘት ከሕዝቡ ጋር የሆነውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 1፡23።

ለ. ታቦቱ ክርስቶስን እንደ ቤተ ክርስቲያን ማዕከል እና ይዘት በማመልከት የማደሪያው ድንኳን ማዕከል እና ይዘት ነበር፤ ታቦቱ በማደሪያው ድንኳን ራእይ በመጀመሪያ የተጠቀሰው መሆኑ የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስ ፊተኛውን ስፍራ መያዙን ነው—ዘጸ. 25፡22፤ ቆላ. 1፡17፣ 18ለ፦

1. ታቦቱ እንደ እግዚአብሔር ምስክር፣ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ መግለጫ እና መገለጥ የሕጉን ጽላቶች ይዟል–ዘጸ. 25፡16፤ 31፡18።
2. በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያለው ታቦቱ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ፣ እንደ የቤተ ክርስቲያን ማዕከል (ኤፌ. 2፡21-22)፣ እና የእግዚአብሔር ቤት የሆነችውን የቤተ ክርስቲያንን ይዘቶች (1 ጢሞ. 3፡15-16፤ ተዛ. 1 ሳሙ. 4፡22፤ ራእ. 3፡20) ያመለክታል።

ሐ. በወርቅ የተለበጠው የግራር እንጨት ታቦት እንደ እግዚአብሔር አካል መልበስ እና እንደ የመለኮት እና የሰብዕና መዋሐድ፣ የእግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንባታ እግዚአብሔርን እንነካው እና እንደሰተው ዘንድ በመንፈሳችን ውስጥ የሚኖረውን እስትንፋሳዊው ክርስቶስ ያመለክታል–2 ጢሞ. 4፡22፤ 2 ቆሮ. 3፡17፤ ቆላ. 2፡9፤ ዕብ. 9፡4፦

1. የግራር እንጨት እግዚአብሔርን ለመግለጥ እንደ መሠረታዊ ንጥረ ነገር በባህሪው ጠንካራ እና በደረጃው ከፍ ያለውን የክርስቶስን ሰብዕና ያመለክታል—ዘጸ. 25፡10፤ ማቴ. 3፡16፤ 4፡4፤ 8፡20፤ 9፡12-13፤ 11፡29፤ 12፡19-20፤ 17፡27፤ 20፡28፤ 27፡12፣ 14፤ ማር. 1፡35፤ 6፡39-41፤ ዮሐ. 6፡12፤ 7፡6፤ ተዛ. ሐዋ. 16፡7።
2. የግራሩ እንጨት በውስጥም በውጭም በወርቅ የተለበጠ መሆኑ መለኮታዊ ባህሪ የሰብዕናን ባህሪ መስረፁ እና በሰብዕና ባህሪ በኩል ይገለጥ ዘንድ በሰብዕና ባህሪ ላይ ማረፉን ያመለክታል—ዘጸ. 25፡11፤ ራእ. 3፡18፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ ተዛ. ራእ. 17፡4።

መ. የታቦቱ የስርየት መክደኛ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር እና እንደ ተዋጁት ሕዝቡ መገናኛ ስፍራ ያመለክታል—ዘጸ. 25፡17-22፦

1. ክርስቶስ የሚያስተሰርየው (ዕብ. 2፡17)፣ በእግዚአብሔር እና በእኛ መካከል ሰላም የሚያደርገው፣ እንደ ማስተሰርያው መሥዕዋት በራሱ በኩል የእግዚአብሔርን ፍላጎት በማሟላት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቀን ነው (1 ዮሐ. 2፡2፤ 4፡10)።
2. ክርስቶስ ከመለኮትነቱ ማብራት እና ከሰብዕናው መዋጀቱ ጋር በእግዚአብሔር ፊት ስርየትን የምንደሰትበት እና እርሱን እንደ ፀጋ ለመቀበል ጻድቅ፣ ቅዱስ እና ክቡር ከሆነው አምላካችን ጋር የምንገናኝበት እና ኅብረት የምናደርግበት የስርየት መክደኛውም ጭምር ነው—ሮሜ 3፡25፤ ዕብ. 4፡16፦

   ሀ. በስርየት መክደኛው ላይ ያሉት ሁለቱ የወርቅ ኪሩቤሎች የእግዚአብሔር ክብር በክርስቶስ ደምቆ እንደሚያበራ ያመለክታሉ (ዘጸ. 25፡18-20)፤ የማስተሰርያው መሥዕዋት ደም በታቦቱ የስርየት ክዳን ላይ መረጨቱ ከክርስቶስ ደም ቤዛነት የተነሣ ከጻድቁ እግዚአብሔር ጋር በክብሩ መካከል ኅብረት ማድረግ እንደምንችል ያመለክታል (ዘሌ. 16፡14-15)።

   ለ. እግዚአብሔር አብልጦ በተገናኘን እና በተናገረን መጠን፣ እና እኛ አብልጠን ከእግዚአብሔር ጋር በተገናኘን እና ንግግሩን ባደመጥን መጠን፣ የእግዚአብሔር ምስክር በልምምዳችን አብልጦ ይኖራል።

**III. የታቦቱ እና የማደሪያው ድንኳን ታሪክ የእግዚአብሔርን ልብ ፍላጎት፣ የቤተ ክርስቲያንን ባድማነት፣ እና ለእግዚአብሔር ምስክር፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ የቤተ ክርስቲያንን ምለሳ ያሳያል—ዘጸ. 25፡9-10፤ 26፡26-30፤ 40፡38፦**

ሀ. እንደ ማደሪያው ድንኳን ማዕከል እና ይዘት፣ ታቦቱ ለእግዚአብሔር የጋራ መገለጥ የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን፣ የእግዚአብሔር ቤት የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ማዕከል እና ይዘት የሆነውን ክርስቶስን ያመለክታል—25፡22፤ 40፡21፤ ቆላ. 2፡9፤ ኤፌ. 2፡21-22፤ 1 ጢሞ. 3፡15።

ለ. በታሪኩ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ታቦቱ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ነበር፤ ይህም ጤናማዋ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን መገለጥ እንደነበረች እና ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ይዘት እንደነበረ ያመለክታል፤ ሆኖም ግን በመጨረሻ ታቦቱ ከማደሪያው ድንኳን ተለይቶ ነበር፤ ይህም የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያን እንደዘቀጠች እና የክርስቶስን እውነታ እና መገኘት እንዳጣች ነው—ዘጸ. 40፡34-35፤ 1 ሳሙ. 4፡1—7፡2።

ሐ. ለኢኮኖሚው መፈጸም መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት ታቦቱ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር አካል መልበስ እና እንደ ሦስታንዱ አምላክ መገኘት ከሕዝቡ ጋር በምሳሌ ያሳያል (ኢያ. 3፡3፣ 10-17)፤ ታቦቱን ማውጣት የእግዚአብሔርን መገኘት ማውጣት ነበር (ዘኍ. 10፡33-36፤ 1 ሳሙ. 4፡3-4)።

መ. የታቦቱ እንቅስቃሴ አካል መልበሱ በሆነው በክርስቶስ በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ስዕል ነበር (መዝ. 68፡1-18)፤ ሆኖም ግን፣ እስራኤላውያን ከፍልስጤማውያን ጋር በሚዋጉበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለመንቀሳቀስ አልፈለገም።

ሠ. የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ሃሳብ ወይም ግድ መሰኘት አልነበራቸውም፣ ፍልስጤማውያንን ለመዋጋት ታቦቱን ማውጣታቸው እግዚአብሔርን አለአግባብ መጠቀማቸውን፣ እንደውም ለደህንነታቸው፣ ለሰላማቸው፣ ለእረፍታቸው፣ እና ለትርፋቸው አብሯቸው እንዲወጣ ማስገደዳቸውን የሚያመለክት ነበር።

ረ. በመርህ፣ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ምንም ትኩረት ሳንሰጥ ለራሳችን ስኬት በምንጸልይበት ጊዜ ሁሉ ተመሳሳይ ነገር እንፈፅማለን፤ እግዚአብሔርን አለአግባብ ከመጠቀም ይልቅ በእግዚአብሔር ልብ መሠረት እና ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መጸለይ፣ መኖር፣ እና እንደ ሳሙኤል አይነት ሰዎች መሆን አለብን።

ሰ. ዛሬ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምስክር በሰዎች ፍላጎት ተክተውታል፤ የሰው ፍላጎት የእግዚአብሔርን ምስክር ሲተካ፣ ዝቅጠት ይጀምራል ችግሮችም ይነሣሉ፤ ታቦቱ የእግዚአብሔር ታቦት ብቻ ሳይሆን (1 ሳሙ. 4፡11፣ 13፣ 17-19፣ 21-22) የምስክሩም ታቦት ነበር (ዘጸ. 25፡22፤ 40፡21)።

ሸ. እስራኤል ንስሐ መግባት፣ በጥልቀት እና በዝርዝር መናዘዝ፣ ከጣዖቶቻቸው ወደ እግዚአብሔር መመለስ፣ እና ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን መጠየቅ ነበረባቸው።

ቀ. ይልቁንም፣ ለእግዚአብሔር መሻት ወይም ለዘላለማዊው ኢኮኖሚው ምንም ልብ ሳይኖራቸው በታቦቱ እንቅስቃሴ በኩል በፊት የተለማመዷቸውን ድሎች መሠረት በማድረግ በታቦቱ ለማመን አጉል እምነታቸውን አንቀሳቀሱ።

በ. ከእስራኤል ዝቅጠት የተነሣ፣ የማደሪያውን ድንኳን ያለምንም እውነታ፣ ያለ ተገቢው ይዘት ባዶ መያዣ አድርጎ በመተው ታቦቱ በፍልስጤማውያን ተማረከ ከማደሪያውም ድንኳን ተለየ (1 ሳሙ. 4፡11—6፡1)፤ ይህ በሁለተኛው ደረጃ ታሪኳ፣ ቤተ ክርስቲያን የዘቀጠች እና የክርስቶስን እውነታ እና መገኘት ያጣች እንደሆነች ያመለክታል (ምዕ. 3—4፤ ራእ. 3፡20)።

ተ. በዝቅጠታቸው እስራኤል ሞኝ ነበሩ ምክንያቱም በቀጥታ በእግዚአብሔር አልታመኑም፤ ይልቁንም በእግዚአብሔር በተወሰኑት ሥርዓቶች ታመኑ፤ የእግዚአብሔርን ታቦት ከማደሪያው ድንኳን ከማውጣታቸው በፊት፣ ኢያሱ በኢያሪኮ እንዳደረገው እግዚአብሔርን መጠየቅ ነበረባቸው (ኢያ. 6፡2-4፤ ተዛ. 9፡14)።

ቸ. ከመንፈሳችን ጥልቀት ለጌታ፣ "ጌታ ሆይ፣ እኔ እዚህ በምድር ላይ ለጤናዬ፣ ለስኬቴ፣ ለደህንነቴ፣ ለሰላሜ፣ ለእረፍቴ፣ ወይም ለትርፌ አይደለሁም፤ ለኢኮኖሚህ መፈጸም ከአንተ ጋር የሚተባበር እውነተኛ ድል ነሺ ናዝራዊ መሆን ስለምፈልግ፣ እኔን በተመለከተ በልብህ ያለውን እጠይቅሀለሁ" ማለት አለብን—1 ሳሙ. 2፡30፣ 35፤ ዘኍ. 6፡1-9፤ ተዛ. 1 ነገ. 8፡48፤ ኤር. 32፡39።

ኀ. የእስራኤል ልጆች በዝቅጠታቸው እግዚአብሔርን ፈፅሞ በደሉ፣ እግዚአብሔርም ተዋቸው፤ በመጨረሻም፣ ታቦቱ እስራኤልን ከማዳን ይልቅ፣ ታቦቱ ራሱ ተማረከ፣ የእግዚአብሔርም ክብር ከእስራኤል ለቀቀ (1 ሳሙ. 2፡30፣ 34፤ 4፡10-18፣ 22፤ መዝ. 78፡61)፤ "ታቦት አልባ" መሆን "ክርስቶስ አልባ" መሆን ነው፣ "ክርስቶስ አልባ" መሆን ነው፣ "ክርስቶስ አልባ" መሆን ማለት "ኢካቦድ" አለ ማለት ነው፣ ትርጓሜውም ክብር የሌለው ማለት ነው (1 ሳሙ. 4፡21-22፤ ራእ. 3፡20)።

**IV. ኋላም፣ ታቦቱ ተመለሰ በመጀመሪያም በቅሪያትይዓሪም ለሃያ ዓመት ወደ ተቀመጠበት ወደ አሚናዳብ ቤት (1 ሳሙ. 6፡2-7፡2)፣ በመቀጠልም ለሦስት ወራት ወደ ቆየበት የጌት ሰው ወደ ሆነው ወደ አቢዳራ ቤት (2 ሳሙ. 6፡1-11፤ ተዛ. 1 ሳሙ. 1፡24፤ ኢያ. 18፡1) መጣ፤ ይህ የሚያመለክተው ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የጌታ መገኘት (ታቦቱ) የነበራቸው ነገር**

**ግን የክርስቶስ መገለጥ (የማደሪያው ድንኳን) የሆነው ተገቢው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሌላቸው ብዙ "አቢዳራዎች" ተነሥተው እንደነበር ነው።**

**V. ዳዊት ታቦቱን ከአቢዳራ ቤት በኢየሩሳሌም በተመረጠው ስፍራ፣ በጽዮን ተራራ፣ በራሱ ከተማ ለታቦቱ ወዳዘጋጀው ድንኳን አንቀሳቀሰው (2 ሳሙ. 6፥12-19፤ 1 ዜና. 15፥1—16፥1)፤ ይህ የተሻለ ሁኔታ ነበር፣ ታቦቱ ግን ገና ወደ ማደሪያው ድንኳን ስላልተመለሰ አሁንም ተገቢ ባልሆነ ስፍራ ነበር፦**

ሀ. ይህ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ፍላጎት ግድ እንደተሰኘው እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር መገለጥ መሠረት ሳይሆን በራሳቸው ምርጫ መሠረት የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት በተግባር ለመለማመድ የሞከሩትን ሌሎች አማኞችን ያመለክታል።

ለ. እነዚህ አማኞች ክርስቶስ ነበራቸው፣ ነገር ግን ክርስቶስ የነበራቸው ተገቢ ካልሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ተግባራዊ ልምምድ ጋር ነበር (በኢየሩሳሌም ባለው በዳዊት ድንኳን የተመሰለው)—ተዛ. 1 ነገ. 3፥3-15።

**VI. በመጨረሻም፣ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም መቅደሱን መገንባት ከፈጸመ በኋላ፣ ታቦቱ ለጤናማው ሁኔታ ሙሉ ምለሳ በመቅደሱ ውስጥ ወዳለው ቅድስተ ቅዱሳን ተንቀሳቀሰ፤ ዛሬ ጌታ በምለሳው ለመገለጡ የክርስቶስ አካል እውነታ በሆነችው በተገቢዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ጤናማ የክርስቶስ ሁኔታ ለመመለስ እየሠራ ነው—8፥1-11፣ 48፤ ኤፌ. 2፥21-22፤ 3፥16-21።**

**VII. የታቦቱ እና የማደሪያው ድንኳን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ አሁን ያለውን ቤተ ክርስቲያንን የሄደችበትን መንገድ እና የቤተ ክርስቲያንን ሁኔታ ሙሉ ስዕል በመስጠት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅድመ-ስእል ነው፤ የዚህ ታሪክ አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች አሉ፦**

ሀ. የመጀመሪያው ሁኔታ ክርስቶስ በውስጧ ያላት ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ይህ ታቦቱ እንደ ይዘቱ እና ማደሪያው ድንኳን እንደ መገለጡ ባለው በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ባለው በታቦቱ ተመስሏል፤ ይህ ፍጹም ጤናማ በሆነ ሁኔታ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ይዘት የመሆኑ እና ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ መገለጥ የመሆኗ የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ደረጃ ስዕል ነው—ዘጸ. 40፥34-38፤ ኤፌ. 3፥16-21።

ለ. ሁለተኛው ሁኔታ በውስጧ ክርስቶስ የሌለባት ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ይህ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መውደቅ የተነሣ ታቦቱ በመማረኩ እና ከማደሪያው ድንኳን በመለየቱ ተመስሏል፤ የማደሪያው ድንኳን ባዶ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን እውነታ እና መገኘት እንድታጣ ያደረጉትን ክርስቲያኖች ውድቀት ያሳያል—ራእ. 2፥4-5፤ 3፥20።

ሐ. ሦስተኛው ሁኔታ ክርስቶስ ያለ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ይህ ታቦቱ ያለ ማደሪያው ድንኳን በመሆኑ ተመስሏል፤ በመጀመሪያ፣ በአሚናዳብ ቤት በቂርያትይዓሪም ለሃያ ዓመታት (1 ሳሙ. 7፥1-2) በመቀጠልም በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት ለሦስት ወር (2 ሳሙ. 6፥10-12)፣ ታቦቱ ከማደሪያው ድንኳን ተለይቶ ነበር፤ ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ አሁን ብዙ አቢዳራዎች እንደነበሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይገልጣል።

መ. አራተኛው ሁኔታ ክርስቶስ ጉድለት ካላት ቤተ ክርስቲያን ጋር ነው፤ ዳዊት በኢየሩሳሌም ውስጥ ለታቦቱ ድንኳን አዘጋጅቶ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለሙሴ በገለጠው ንድፍ መሠረት አልነበረም፤ ብዙ ክርስቲያኖች ታቦቱ—ክርስቶስ—ጉድለት ያላት ቤተ ክርስቲያን ጋር አላቸው—ቁ. 17፤ 1 ዜና. 15፥1፤ 2 ዜና. 1፥4፤ ዘጸ. 25፥9።

ሠ. አምስተኛው ሁኔታ ክርስቶስ ከተገቢዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ነው፤ ይህ መቅደስ ለመሆን ከተለቀው እና ከጨመረው ከተገቢው የማደሪያ ድንኳን ጋር በታቦቱ ተመስሏል፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ—ክርስቶስ እንደ እውነታ መገለጡ ከሆነች ከተገቢዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር—ነው ሙሉ ለሙሉ በቤት እንደሆንን የሚሰማን–መዝ. 90፥1-2፤ 91፥1-16፤ 92፥12-15፤ 132፥5፣ 8፤ 1 ዜና. 28፥11-20፤ 2 ዜና. 3፥1።

*© 2021 Living Stream Ministry*